ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ

Tserha Aryam Kidist Selassie
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Minneapolis, Minnesota

ቁጥር 006/09/2015

ቀን መስከረም ፲፬ ቀን ፳፻፲፭

# አባ ምሕረት ዘውዴ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እግር ሥር ወድቀው ይቅርታ ጠየቁ

«ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ ዘንድ
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን» ፪ ተሰ. ፫፡፮

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይኸን መልእክት ያስተላለፈው ማንኛውም ሰው ከሐዋርያት እንደተቀበለው ወግና ሥርዓት ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን መመሪያ ውጪ በሆነ መንገድ አዲስ ሥርዓት መሥርቶ በእራሱ ማስተዋል በመደገፍ ከሚንቀሳቀሰው ሰው ጋር ኅብረት እንዳይኖረን ነው። ይኸንንም መልእክት በሰው ፈቃድ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን በማለት አጽንቶታል። በመሆኑም በሐዋርያት እግር ተተክተው የሃይማኖት መሪነትን መንፈሳዊ ሥልጣን የተረከቡት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጉባኤ ሠርተው ከሃይማኖት መንገድ የተለዩትን ከቅዱስ መጽሐፍ ማስረጃ በመጥቀስ ላቀረቡት የመከራከሪያ ነጥብ አንድ በአንድ መልስ በመስጠት ጥፋታቸውን አውቀውና ከስህተታቸው ተምረው እንዲመለሱ ዕድሉን አዘጋጅተዋል።

ክብር ይግባውና ጌታችን፣ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ» (ሉቃ. ፲፫፡፫) በማለት እንደጻፈልን ባጠፉት ጥፋት ተጸጽተውና ከስህተታቸው ተመልሰው ወደ ቀደመው ሃይማኖታዊ መንገድ በሥርዓቱ ለመገዛት ፈቃደኛ ያልሆኑት ምንደኞችን ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሥልጣናቸው አውግዘው ለይተዋቸዋል። ቤተ ክርስቲያንም በዘመናት ጉዞዋ የመገዘት ሥልጣኑ ያላቸው ሊቃነ ጳጳሳት ሥርዓት ያፈረሱትንና ለመታዘዝ ፈቃደኛ ያልሆኑትን በሕግ መንፈሳዊ በመመራት ሲያወግዙ፤ እንዲሁም በጸጸትና በይቅርታ የሚመለሱትንም ሲፈቱ ኖረዋል። ውግዘት ሥልጣን ማሳያ ሳይሆን ከሥርዓት ያፈነገጡትን ማስተካከያ በመሆኑ ተጸጽተው ለሚመለሱ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የተከፈቱ በሮችና የተዘረጉ እጆች አሏት። ውግዘትን አውጋዡ ሊቀ ጳጳስ በተሰጠው ሃይማኖታዊ ሥልጣን የሚፈጽመው፣ ተወጋዡም ውግዘት ያደረሰበትን ሊቀ ጳጳስ ትክክለኛነት አውቆ በሃይማኖት መንገድና ሥርዓት ይቅርታ በመጠየቅ እንደየደረጃው የሚያስመልሰው ነው። ከዚህ ውጪ ግን ተወግዞ አልተወገዝኩም፤ ሥልጣነ ክህነቱ ተይዞበት አልተያዘብኝም የሚል በእራሱ እና በምእመናኑ ሕይወት የፈረደ ወደ ከፋም ጥፋት የሚሮጥ ነው። በየትኛውም ዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ አሠራር ሥልጣን የሚሰጥ ክፍል አለ፤ ከሥልጣንም የሚሽር አካል አለ። ሥርዓተ ጥምቀት መፈጸም፣ ቀድሶ ማቁረብ፣ ንስሐ መቀበል፣ መስቀል ማሳለም፣ እግዚአብሔር ይፍታህ ማለትና ሌሎችም ተመሳሳይ አገልግሎቶች የሚፈጸሙት ሥልጣን ባለው ካህን እንጂ ሥልጣነ ክህነቱ በተገፈፈበት ካህን የሚፈጸም አይደለም። ምእመናን ይኸንን እያወቃችሁ ልጆቻችሁን ክህነት በሌላቸው ሰዎች በማስጠመቅ እንዳትሳሳቱ አደራ እንላለን።

በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክህነት አገልግሎት ይዘው የሚያገለግሉ ካህናት ደግሞ የብዙዎች እረኛ ናቸውና ለበጎቹ ምሳሌ በመሆን ከእነርሱ በላይ ያሉ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሲያወግዙ ውግዘቱን ተቀብሎ ከጥፋቱ ታርሞ እንደገና ወደ ቀደመው የክህነት ክብር

መመለስ ይገባል እንጂ በብልሃት ከውግዘት ለማምለጥ በየጊዜው አዳዲስ ቀመር እያወጡ ዕድሜ ለማራዘም መሞከሩ ከየትም አያደርስም። ይልቁንስ ለመንጋው ምሳሌ ለመሆን ክህነትን ከሰጠ ሊቀ ጳጳስ ቀኖናን ተቀብሎ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት መጓዙ አማራጭ የሌለው በቸኛ የቤተ ክርስቲያን ሕግ ነው።

ለብዙዎች መልካም ምሳሌ በመሆንና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የቀናች ሃይማኖታዊ መንገድ በመረዳት መልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴ ሰኔ ፲፪ ቀን ፳፻፲ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ሃይማኖትና ሥርዓት የሚጻረር ትምህርት በቀድሞው የሚኒያፖሊስ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በመስጠታቸው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እና ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል እንዲሁም በዳላስ ቴክሳስ አባ ምሕረት ዘውዴን ጨምሮ ሰድስት አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪና አገልጋይ ካህናት ባሉበት ክህነታቸው እንዲያዝ ምክንያት የሆነውን ጥፋታቸውን በዝርዝር አምነውና ተቀብለው የተያዘባቸውን ክህነት እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሥርዓት በታላቅ ትሕትና ዝቅ ብለው ሥልጣነ ክህነቱን በያዙባቸው በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እግር ሥር በመውደቅ የይቅርታ ዕድል እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል። ብፁዕ አቡነ ዘካርያስም የውግዘቱን ደብዳቤ ባስተላለፉበት ወቅት «ጥፋቱን ጥፋት ነው በማለት ተመልሻለሁ ይቅርታ ያድርጉልኝ ብለው ከጠየቁ የያዝኩትን ሥልጣነ ክህነት እለቃለሁ» ባሉት መሠረት መልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴ መስከረም ፲/፳፻፲፫ ዓ.ም. ያለ ምንም ማንገራገርና ማመንታት ጥፋታቸውን ስለአመኑ የቀደመ የክህነት ሥልጣናቸውን ተመልሶላቸዋል።

የተመረጡትንና ታላላቆቹን ሁሉ እስከሚያስት ድረስ መልኩን እየለዋወጠ የሚመጣ ፈታኝ ዲያብሎስ አዳምን ከገነት እንዳወጣው ዛሬም ብዙዎችን እየፈተነና ከሃይማኖት መንገድ እያሰናከለ ከክህነታቸው ሲያስወጣቸው እናያለን። አባ ምሕረት ዘውዴ ግን በኖሩበት የሃይማኖት ጎዳና ተፈትኖ መውደቅን፣ ወድቆ መነሣትን፣ ጠፍቶ መመለስን ሲያስተምሩ የኖሩ ናቸውና ትናንት የሊቀ ጳጳሱን ትእዛዝ መቀበል ከብዷቸው ግራ ቀኙን ሳይመለከቱ በችኩልነት ከገቡበት አዘቅት ለመውጣት ያለው አማራጭ <u>አንድ ብቻ</u> በመሆኑ ተመልሶ በክህነት ክብር ገብቶ እየቀደሱና እያስተማሩ ብዙዎችን ወደ ክርስትና ለመመለስ ያሉትንም ለማጽናት ብዙ እንደሚጠበቅባቸው አውቀው ክህነታቸውን አስመልሰዋል።

ሃይማኖት የሚገለጸው አጥፍቻለሁ በድያለሁ በማለት በንስሐና በጸጸት በመሆኑ የዕድሜ ባለፀጋ አባት ከሃይማኖት የበለጠ መንገድ ባለመኖሩ እንደሌሎች ሳይታበዩና ውስጥ ውስጡን በመሄድ ክህነቴን መልሱልኝ በአደባባይ ደግሞ ምንም ጥፋት የሌለብኝ ነኝ ሳይሉ ሁሉን በፊት ለፊት አድርገው የሊቃነ ጳጳሳቱንና አብረዋቸው የሚያገለግሉትን ካህናት ድምፅ በመስማት ልባምነታቸውን አሳይተዋል።
መስከረም ፲/፳፻፲፫ ዓ.ም. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃነ ጳጳሳት ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እና ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል እንዲሁም በዳላስ ቴክሳስ አባ ምሕረት ዘውዴን ጨምሮ የአምስት አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪና አገልጋይ ካህናት ባሉበት ክህነታቸው ተይዞባቸው የነበረው መልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ሆኖ በተላከው ደብዳቤ ተነሥቶላቸዋል።

Tserha Aryam Holy Trinity Ethiopian Orthodox Tewahedo Church in Minnesota

መልአከ አርያም አባ ኃይለሚካኤል ሙላት /ቆሞስ/
በኢ.ኦ.ተ. የሚኒሶታ ጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ
Melake Aryam Abba Hailemichael Mulat /Qomos/
Administrator of Tserha Aryam Holy Trinity
Ethiopian Orthodox Tewahedo Church, in Minnesota

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን
የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅ እና
የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሃገረ ስብከት
ጽሕፈት ቤት

The Ethiopian Orthodox Tewahedo Church
Archdiocese of New York, Northeast, Southeast and
Central United States of America

ቀን 09/25/2015
ቁጥር 128

ለጽርሐ አርያም ቅድስት ሥላሴ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን
ሚኒያፖሊስ፣ ሚኒሶታ

ጉዳዮ፦ <u>የመልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴን ይቅርታ መጠየቅና የታገደው ሥልጣነ ክህነታቸው መመለስን ይመለከታል</u>

ሰኔ ፲፪ ቀን ፳፻፯ ዓ.ም. መልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴ በቀድሞው ሚኒያፖሊስ ደብረ ሰላም መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በመገኘት ለምዕመናን ማሰናከያ የሚሆን ትምህርት በማስተላለፋቸው፣ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስን ትዕዛዝ በመተላለፋቸው፣ የታላቁ ዋልድባ ገዳምን ክብር የሚዳፈር ቃል በመናገራቸውና የፍትሃ ነገሥቱን ቃል እንደራሳቸው ሃሳብ በመተንተናቸው ምክንያት ጥፋተኛነታቸውን አምነው ይቅርታ እስኪጠይቁ ድረስ ሥልጣነ ክህነታቸው መያዙ ይታወሳል።

መስከረም ፲ ቀን ፳፻፰ ዓ.ም. በዳላስ ከተማ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የሰሜን ምሥራቅ የደቡብ ምሥራቅና የመካከለኛው አሜሪካ የኒውዮርክ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል፣ ብፁዕ አቡነ ፋኑኤል የዋሽንግተን ዲሲና ካሊፎርኒያ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል፣ እንዲሁም ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ ሆኖ በተላከው ቃለ ጉባኤ ላይ የተዘረዘሩት በዳላስ የሚገኙ ስድስት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎችና አገልጋይ ካህናት በተገኙበት መልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴ በዝርዝር ለቀረቡላቸው ነጥቦች በሙሉ ጥፋተኛነታቸውን ስለአመኑና በፍፁም ትህትና ይቅርታ ስለጠየቁ ተይዞባቸው የነበረው ሥልጣነ ክህነት የተመለሰላቸው መሆኑን እንድታውቁት ይሁን።

ሰኔ ፲፪ በተሰጠውና በተለያየ ስሌዳ ላይ ተለጥፎ በሚገኘው፣ ይቅርታም በተጠየቀበት የስህተት ትምህርት እንዳይሰናከሉ ይህ መልዕክት ለመላ ምዕመናን እንዲደርስ እንድታደርጉና በዐውደ ምህረት እንድታስተላልፉት እናሳስባለን።

እግዚአብሔር ከሁላችን ጋር ይሁን፤ የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤት አይለየን።

ብጹዕ : አባ: ዘካርያስ : በኢትዮጵያ : ኦርቶዶክስ ተዋህዶ
ቤተክርስቲያን : በሰሜን : ምስራቅና : ምዕራብ አሜሪካ
የንዮርክ : ሀገረ : ስብከት : ሊቀ : ጳጳስ :

Abba Zekarias Archbishop of Ethiopian
Orthodox Tewahedo Church Diocese of
New York in Northeast and West U.S.

140-142 W 176th Street Bronx, New York 10453
Tel. 718-466-0600/718-299-2741 Fax 718-466-1271

የስብሰባው አጀንዳዎች

በሚኒሶታ ደብረሰላም መድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን መልአከ ምሕረት በሰጡት ትምህርት ላይ

1.አምስት ሥላሴ ተብሎ ልድ መልክ ስለቀረበው ጉዳይ

2.ዘጠኝ መለኮት የሚያምኑ አሉ ይባላል ብለው ስለተናገሩት ጉዳይ

3.ም ዕምናን ሁላችሁ ጳጳሳት ናችሁ ስለተባለው ጉዳይ

ከላይ በርዕሱ የተጥቀሱትን ጉዳዮች በትምሕርታቸው ጣልቃ አስገብተው በምሳሌ መልክ በማቅረባቸው የተሳሳተ ግንዛቤን በሕዘብ አዕም በማስረጻቸው መልአከ ምሕረት ዘውዱ በጉባዔው ፊት ቆመው ስለ እነዚህ ጉዳዮች ማብራሪያ እንዲሰጡ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በብጹዕ አቡነ ፋኑኤል ተጠይቀው መልሳቸውን እንደሚከተለው አቅርበዋል።

1.በኢትዮጵያ ሀገራችን ያለውን የኑሮ ውድነት ለመግለጽ < አንድ የሀዳና ሰው ስለ አምስቱ ሥላሴ እያለ ደጋግሞ ሲለምን የሰማ አንድ መንገደኛ ሰው ፤ አንተ ከመቼ ጀምሮ ነው ሥላሴ አምስት የሆኑት ቢለው ፤ ዘንድሮ ምን ያልጨመረ ነገር አለ> ?ብሎ መለሰ ብለው ለም ዕመናን ያቀረቡት ቀልድ ከቤተ ክርስቲያን የምስጢረ ሥላሴ አስተምህሮ አንጻር በቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምሕረት የማይነገር ቀልድ በመሆህን ይህንን መናገሬ ፍጹም ስህተት ነው በማለት ያስተላለፉት ምሳሌያዊ መልእክት ስህተት መሆኑን አምነው ይቅርታ ጠይቀውብታል ።

2. በዋልድባ ያሉ መነኮሳትን ክብር የሚነካው ዘጠኝ መለኮት አለ ብለው የሚያምኑ የገዳሙ መነኮሳት አሉ በማለት ሲባል ከመስማት ውጪ በቦታው ተገኝተው በትምህርት ማረጋገጫ ያለገኙለትን የይባላል አነጋገር በይባላል ብቻ ማቅረባቸው ስህተት መሆኑን አምነው ይቅርታ ጠይቀዋል ።

3. ምእመናን ሁላችሁ ጳጳሳት ናችሁ ተብሎ ለምእመናን የተነገረው መልእክትና ውግዘትን በኃይል መሻር ትችላላችሁ ተብሎ የተነገረው መልእክት አባባሉ ፍጹም ስህተት መሆኑን በማመን ይቅርታ ጠይቀዋል ።

ከላይ የተጠቀሱትንና በአጠቃላይ ለምእመናን ማሰናከያ ሆነዋል የተባሉ በትምህርቱ የተላለፉ መልእክቶችን መናገሬ ከሀገረ ስብከቱን ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ፈቃድ ውጪ ለፈጸምኩት ስህተት ይቅርታ እጠይቃለሁ በማለት በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ እግር ሥር በመውደቅ ይቅርታ የጠየቁ ሲሆን ፤ ብፁዕ አባታችን አቡነ ዘካርያስም ይቅር ብያለሁ በማለት አባታዊ ፍቅራቸውን አሳይተዋል ። ከዚህ በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ በኢንተርኔት የተለቀቀው ትምህርት ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ከተለጠፈበት ሰሌዳ ላይ እንዲነሣ ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ጉባዔውን ጠይቀዋል ። በተጨማሪ ብፁዕነታቸው ቀደም ሲል ከላይ በተዘረዘሩት ስህተቶች ምክንያት ያስተላለፉትን የክህነት እገዳ ደብዳቤ የሻሩና ያነሱ መሆናቸውን አረጋግጠዋል ።

ቀን መስከረም 10 2008 ዓም

ጉዳዩ - በሜኖሶታ ደ/ሰ/መድኃኔ ዓለም ቤ/ክ መልአከ ምሕረት ዘውዴ ስላስተላለፉት መልዕክትና ትምህርት

በስብሰባው ላይ የተገኙ

1. ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የኒውዮርክና የምሥራቅ ሰሜን አሜሪካ ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል
2. ብጽዕ አቡነ ፋኑኤል የዋሺንግተን ዲሲና ካሊፎርኒያ አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና የቅዱስ ሲኖዶስ አባል
3. መልአከ ፅሐይ ቀሲስ ታደሰ አርአያ የቴክሳስ ግዛት ሊቀ ካህናትና የደብረ ፀሐይ ተክለ ሃይማኖት ወአቡነ አረጋዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
4. መልአከ ብርሃን ቀሲስ መስፍን ደምሴ የቴክሳስ ሀገረ ስብከት ዋና ጸሐፊና የደብረ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
5. መልአከ ምሕረት አባ ምሕረት ዘውዴ የቴክሳስ ሀገረ ስብከት ስብከተ ወንጌል ኃላፊና የመካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ወቅድስት ኪዳነ ምሕረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ
6. መል አከ ፀሐይ አባ ሐዋዝ የደብረ መንክራት ቅዱስ ጊዮርጊስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደሪ
7. መጋቤ ሃይማኖት አባ የማነ ብርሃን ወልደ ሳሙኤል የደብረ ፀሐይ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወአቡነ አረጋዊ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን
8. ቀሲስ የማነ ብርሃን ገዳ የመካነ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ወቅድስት ኪዳነ ምሕረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ካህን

